23ኛ ዓመት ቁጥር 12
23th Year No 12

ባህር ዳር መጋቢት 22 ቀን 2010 ዓ.ም
Bahir Dar 31st Day of April, 2018

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት
ዝክረ-ሕግ
ZIKRE-HIG
OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE IN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

የአንዱ ዋጋ ብር 175.00 Unit Price	በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ	ISSUED UNDER THE AUSPICES OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE	የፖ.ሣ.ቁ. 312 P.O.Box

ማውጫ	CONTENTS
ደንብ ቁጥር 166/2010 ዓ.ም በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የተሻሻለው የደን ኢንተርፕራይዝ ማቋቋሚያ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ	Regulation No. 166/2018 The Revised Amhara National Regional State Forestry Enterprise Establishment, Council of Regional Government Regulation
ደንብ ቁጥር 166/2010 ዓ.ም በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የተሻሻለው የደን ኢንተርፕራይዝን ለማቋቋም የወጣ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ	REGULATION NO. 166/20180 A REVISED REGULATION ISSUED BY THE COUNCIL OF THE REGIONAL GOVERNMENT TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE FORESTERY ENTERPRISE IN THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE

ክልሉ በደን ልማት ረገድ ያለውን ጂኦ-ኢኮሎጂያዊ አቅም ተጠቅሞ የደኑ ዘርፍ ለነዋሪው ህዝብ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገት መፋጠን ተፈላጊውን አስተዋጽኦ ሊያበረክት የሚችልበትን እድል ማመቻቸት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

Whereas, it has been found necessary that the region, having utilized its geo-ecological potential with regard to the forestry development, has to facilitate an opportunity for the forestry sector to enable it to make a contribution required of it for the acceleration of the economic and social development of the people therein;

በክልሉ ውስጥ ለሚቀረፁት የደን ልማት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ ዘርፉ ራሱ በቂ ሃብት የሚያመነጭበትን ተቋማዊ ስርአት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

Whereas, it has become necessary to put in place an institutional system whereby the sector itself would generate adequate resource for the execution of the forestry development programs and projects to be formulated in the Regional State;

በክልሉ ውስጥ በተለያዩ ሥፍራዎች ለምተው የሚገኙት የመንግሥት ደኖች ለአካባቢው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ያደርጉ ዘንድ በአግባቡ ጥቅም ላይ ማዋል ተገቢ በመሆኑ፤

Whereas, it has become appropriate to properly put to use those public forests which are developed and found at various places throughout the Region so that they shall make a contribution to the locality with respect to the latter's social and economic development thereof;

በክልሉም ሆነ በሀገር አቀፍ ደረጃ በእንጨትና በእንጨት ውጤቶች አቅርቦትና ፍላጎት መካከል ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ የመጣውን ክፍተት ለመመላት ጠንካራ የደን ልማት አደረጃጀት መፍጠር በማስፈለጉ፤

Whereas, with a view to filling the ever increasing gap between supply and demand in wood and wood products at the regional and national levels from time to time, it is necessary to create a strong forestry development structure thereof;

በክልሉ ውስጥ ክፉኛ ተራቁቶ የሚታየውን የመሬት ክፍል በደን በመሸፈን የአካባቢ ተሃድሶን ማምጣትና መሬቱን ለተሻለ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም እንዲውል ማድረግ ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፤

Whereas, it has become appropriate to bring about an environmental rehabilitation and cause the land to be used for better economic benefits by covering that part of the land which has been adversely degraded in the region with afforestation thereof;

በሥራ ላይ ያለውን ኋላቀር የደን ልማትና አጠቃቀም ሥርዓት ሳይንሳዊና ቀልጣፋ በሆነ አስተዳደር የሚተካ ሞዴል በመፍጠር አሠራሩን ማሻሻልና ዘመናዊ ማድረግ በማስፈለጉ፤

Whereas, it has been necessary to revise and modernize the working system by creating a model which is bound to replace the existing, outdated forestry development system in a scientific and efficient administration;

በክልሉም ሆነ በሀገር አቀፍ ደረጃ ሲታይ የግሉ ዘርፍ በደን ልማትና ኢንቨስትመንት ረገድ የሚያሳየው ተሣትፎ አናሳ ከመሆኑ የተነሳ የመንግሥትን ቀጥተኛ ተሣትፎ የሚጠይቅ ስለሆነ ራሱን የቻለና ንብረትነቱ የክልሉ መንግሥት የሆነ የደን ልማት ኢንተርፕራይዝ ማቋቋምና በተወዳዳሪነት እንዲሠራ ማድረግ በማስፈለጉ፤

Whereas, when evaluated both at the regional and national levels, due to the fact that the participation of the private sector in the forestry development and investment is insignificant, and such a condition thus requires the direct involvement of the government, it has been necessary to establish a forestry development enterprise which is autonomous and owned by the Regional State as well as cause same to operate in a competitive way;

ከዚሁ ጎን ለጎን በሁሉም የክልሉ አካባቢዎች እየተበራከተ የመጣውን ሥራ-አጥነት ለመቀነስ ይቻል ዘንድ ሰፊ የሥራ እድል መፍጠር የሚያስችል የደን ልማት ማካሄድ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

Whereas, alongside this, it has been found necessary to carry out vast development efforts that would enable to create a multitude of job opportunities with a view to reducing the ever growing unemployment in all areas of the Region;

የክልሉ መንግስት የልማት ድርጅቶች አመሰራረት፣ አደረጃጀት፣ አመራርና ድጋፍ አሰጣጥ አዋጅ ቁጥር 236/2008 ዓ.ም ከመውጣቱ በፊት ተቋቁመው ሲሰሩ የቆዩ የልማት ድርጅቶች እንደገና በደንብ እንዲደራጁና በተቀናጀ መንገድ እንዲመሩ በዚሁ አዋጅ የተደነገገ በመሆኑ፤

Whereas, it has been stipulated that the public enterprises which have been established and become operational prior to the enactment of the Regional Public Enterprises' Establishment, Organization, Management and Support-Provision Proclamation No. 236/2016 shall be re-established by regulation and managed in an integrated way in accordance with the said proclamation;

የአማራ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት በተሻሻለው የብሄራዊ ክልሉ ህገ-መንግስት አንቀጽ 58 ንኡስ አንቀጽ (7)ና በክልሉ የመንግስት ልማት ድርጅቶች አመሰራረት፣ አደረጃጀት፣ አመራርና ድጋፍ አሰጣጥ አዋጅ ቁጥር 236/2008 ዓ.ም አንቀጽ 46 ንኡስ አንቀጽ (1)ና አንቀጽ 49 ንኡስ አንቀጽ (1) ድንጋጌዎች ሥር በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

Now, Therefore, the Council of the Amhara Regional Government, in accordance with the powers vested in it under the provisions of Art. 58, sub. Art. (7) of the Revised Regional Constitution and Art. 46 Sub Art. (1) and Art. 49 Sub-Art. (1) of the Regional Public Enterprises Establishment, Organization, Management and Support-Provision Proclamation No. 236/2016, hereby issues this regulation.

ክፍል አንድ
ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የተሻሻለው የደን ኢንተርፕራይዝ ማቋቋሚያ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 166/2010 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ

1. የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፣

ሀ. **"ደን"** ማለት በተፈጥሮ የበቀሉ ወይም ተተክለው የለሙ በአብዛኛው የዛፎችና ሌሎች የእንጨትነት ጠባይ ያላቸው ተክሎች የሚገኙበት የእጸዋት ክምችት ነው።

ለ. **"ዛፍ"** ማለት በዓይነቱ በዕድሜውና በመጠኑ ሳይለይ የእንጨትነት ጠባይ ያለው ሲሆን ቀርቀሃ፣ ዘንባባና ኢንተርፕራይዙ ዛፍ ብሎ የሚሰይመውን ማናቸውንም ተክል ሊጨምር ይችላል።

ሐ. **"የደን መሬት"** ማለት ለደን ልማትና ጥበቃ ተብሎ የተከለለና በደን የተሸፈነ አካባቢ ሲሆን የቁጥቋጦ መሬትንና በከፍተኛ ተዳፋት ላይ የሚገኙና የተራቆቱ መሬቶችን ይጨምራል፡

መ. **"የመንግሥት ደን"** ማለት በክልሉ መንግሥት ባለቤትነት ሥር የዋለ ማናቸውም ጥብቅ ወይም ምርት ሰጪ ደን ነው።

PART ONE
GENERAL

1. Short Title

This regulation may be cited as "The Revised Forestry Enterprise Establishment, Council of Regional Government Regulation No. 166/2018."

2. Definitions

1. Unless the context requires otherwise, in this regulation:

A. "**Forest**" shall mean a collection of plants in which the majority of trees and other plants of a wooden character are found, having either naturally grown or being planted and developed, as the case may be.

B. "**Tree**" shall mean any such thing that has a characteristic of wood without categorization as to its type, age and size and may include bamboo, palm tree and any plant that the Enterprise may designate as such.

C. "**Forestland**" shall mean an area which is reserved for the development and protection of forest and thereby covered therewith and may include shrub lands as well as those areas situated at highly sloppy and degraded lands.

D. "**Government Forest**" shall mean any reserve or productive forest which is under the ownership of the Regional State.

ሠ. **"የደን ውጤት"** ማለት ዛፍ ወይም የዛፍ ተፈጥሯዊ አካል የሆነ ወይም እንጨት ያልሆነ ማናቸውም ምርት ወይም በመጀመሪያ ደረጃ በሰው እጅ የተመረተ ወይም በፋብሪካ የተዘጋጀ የደን ምርት ነው።

E. "**Forest Product**" shall mean any product of a tree or natural part thereof or a non-wood one or a forest product manually made on a primary level or processed by a factory.

ረ. **"ኢሴንሻል ዘይት"** ማለት የተፈጥሮ ሽታማነት ወይም መርዛማነት ካላቸዉ የዛፍ ዝርያዎች ወይም የሳር ዝርያዎች ተጨምቆ፣ ተቀቅሎ ወይም ተፈጭቶ የሚመረት ሲሆን ለኢንዱስትሪ እቃነት የሚያገለግል የደን ወይም የዕጽዋት ምርት ዉጤት ነው።

F. "**Essential oil**" shall mean the byproduct of forest or plant which would be produced from species of tree having natural odor or poison or from species of trees or grass through squeezing, boiling or grinding used for industrial goods.

ሰ. **"ባዮ-ፊዩል"** ማለት ዕጽዋትን በማብላላት፣ በማዋሀድ ወይም በመጭመቅ የሚገኝ የነዳጅ አይነት ነው።

G. "**Bio-fuel**" shall mean a kind of petroleum to be extracted from plants through fermentation, mixing up or squeezing thereof.

ሸ. **"ባለስልጣን"** ማለት የክልሉ መንግስት ልማት ድርጅቶች ድጋፍና ክትትል ባለስልጣን ነው።

H. "**Authority**" shall mean the Regional Public Enterprises' Support and Follow-up Authority

"አዋጅ" ማለት የክልሉ መንግሥት የልማት ድርጅቶች አመሰራረት፣ አደረጃጀት፣ አመራርና ድጋፍ አሰጣጥ አዋጅ ቁጥር 236/2008 ዓ.ም ነው።

I. "**Proclamation**" shall mean the Regional Public Enterprises' Establishment, Organization, Management and Support-Provision Proclamation No. 236/2016.

ቸ. **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።

J. "**Person**" shall mean any natural or juridical person.

2. በዚህ ደንብ ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል።

2. All provisions of this regulation set out in the masculine gender shall also apply to the feminine gender.

ክፍል ሁለት

ስለደን ኢንተርፕራይዝ መቋቋም፣ ተጠሪነት፣ ዓላማና ስልጣን

3. ስለ መቋቋምና ተጠሪነት

1. የኢንተርፕራይዙ ተጠሪነት ለባለስልጣኑ ይሆናል፡፡

2. በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት የደን ኢንተርፕራይዝ /ከዚህ በኋላ "ኢንተርፕራይዙ" እየተባለ የሚጠራው ራሱን የቻለና ህጋዊ ሠውነት ያለው የክልሉ መንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ እንደገና ተቋቁሟል፡፡

4. ስለ ካፒታል

የኢንተርፕራይዙ የተፈቀደ ካፒታል ብር 76,339,163.00 (ሰባ ስድስት ሚሊዮን ሶስት መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ሺህ አንድ መቶ ሰላሳ ሶስት ብር) ሲሆን በአይነት ደግሞ የክልሉን መንግሥት ደኖች ተጨማሪ መስሪያ ካፒታል አድርጎ የተቋቋመ ነው፡፡

5. የኢንተርፕራይዙ ዓላማዎች

ኢንተርፕራይዙ በዚህ ደንብ መሰረት የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

1. ደንና የደን ውጤቶችን በስፋት በማልማት፣ በማምረትና እሴት በመጨመር የክልሉን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት ማፋጠን፤

PART TWO

ESTABLISHMENT, ACCOUNTABILITY, OBJECTIVES AND POWERS OF THE FORESTERY ENTERPRISE

3. Establishment and accountability

1. The Enterprise shall be accountable to the Authority.

2. The Amhara National Regional State Forestry Enterprise /hereinafter referred to as "**The Enterprise**"/ is hereby re-established under this regulation as an autonomous public enterprise of the Regional State, having legal personality.

4. Capital

The Enterprise is hereby established having secured the allocation of the authorized capital totaling Birr 76, 339, 163.00 (seventy six million, three hundred thirty nine thousands and one hundred sixty three Birr) and with the regional government's forests in kind as an additional working capital, as well

5. Objectives of the Enterprise

The Enterprise shall, pursuant to this regulation, have the following objectives:

1. To accelerate the economic and social development of the region by extensively developing and producing forest and forest products as well as by increasing the value of same;

2. ሰፊ የሥራ ዕድል በመፍጠር ሥራ አጥነትን መቀነስና የክልሉን ህብረተሰብ ዘላቂ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፤

3. በክልሉም ሆነ በሀገር አቀፍ ደረጃ በእንጨትና በእንጨት ውጤቶች አቅርቦትና ፍላጎት መካከል ከጊዜ ወደጊዜ እያደገ የመጣውን ክፍተት ማጥበብና

4. ደንና የደን ውጤቶችን እሴት በመጨመር አምርቶ ወደውጭ በመላክና ከውጭ የሚገቡትን በሀገር ውስጥ ምርቶች በመተካት የውጭ ምንዛሪ አቅምን ማዳበር፡፡

2. To curtail the level of unemployment and thereby ensure the sustainable gains of the Regional Community by creating wider job opportunities;

3. To narrow the ever growing gap, from time to time, between supply and demand in wood and wood products at the regional and national levels;

4. To boost the foreign exchange capacity by producing forest and forest products with an increase in value, exporting them and substituting imported ones with same.

6. ዋና መስሪያ ቤት

የኢንተርፕራይዙ ዋና መስሪያ ቤት በባህር ዳር ከተማ ውስጥ ሆኖ እንዳስፈላጊነቱ በሌሎች የክልሉ አካባቢዎችም ሆነ በመላ ሀገሪቱ የማምረቻና የመሸጫ ቅርንጫፍ ወይም ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤቶችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

6. Head Office

The Head Office of the Enterprise shall be in the City of Bahir Dar; provided, however, that it may establish manufacturing and sales' branches or coordinating offices in any area of the Region and/or the country, as deemed necessary.

7. የኃላፊነት ወሰን

ኢንተርፕራይዙ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ ሊሆን አይችልም፡፡

7. Extent of Liability

The Enterprise may not be liable for the debt in excess of the total asset it possesses.

8. የኢንተርፕራይዙ መዋዕለ ዘመን

ኢንተርፕራይዙ የተቋቋመውና በስራ ላይ የሚቆየው ላልተወሰነ ጊዜ ነው፡፡

8. Life Time of the Enterprise

The Enterprise is established and lasts for an indefinite period of time.

9. የኢንተርፕራይዙ ስልጣንና ተግባር

ኢንተርፕራይዙ በዚህ ደንብ መሰረት የሚከተሉት ዝርዝር ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

9. Powers and duties of the Enterprise

The enterprise shall, pursuant to this regulation, have the following specific powers and duties:

1. ለማገዶ፣ ለኮንስትራክሽንና ለፋብሪካ ፍጆታ በጥሬ ዕቃ ምንጭነት የሚያገለግሉና የተለያዩ የዛፍ ዝርያዎች ተከላ ቦታዎችን ያቋቁማል፣ ያለማል፤

2. በክልሉ መንግሥት ይዞታ ስር ከሚገኙት ደኖች ውስጥ ለምርት የሚሆኑትን ተረክቦ ተገቢውን የማኔጅመንት ፕላን በማዘጋጀት በጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤

3. ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸውን ደኖች ለማልማት የሚያስችሉ የደን መሬቶችን በመለየት ጉዳዩ በሚመለከተው አካል ፈቃድ ተረክቦ የማልማት ሥራ ያከናውናል፤

4. የዱር መ·ጫ፣ እጣን፣ ባዮ-ፊውልና ኢሴንሻል ዘይት በማምረትና በማዘጋጀት ረገድ የንግድ-ሥራዎችን ያካሂዳል፤

5. እንጨትንና እንጨት ያልሆኑ የደን ውጤቶችን ወደተለያዩ የምርት ዓይነቶችና ደረጃዎች የሚቀይሩ ፋብሪካዎችንና ኢንዱስትሪዎችን በማቋቋም ምርቶቹን ለሀገር ውስጥም ሆነ ለውጭ ገበያ ያቀርባል፤

6. የዛፍ ዘር፣ የማስጌጫና ሌሎች የዛፍና ቁጥቋጦ ችግኞችን ያለማል፣ በነዚሁም ይነግዳል፤

7. በእጣንና በመ·ጫ ዛፎች የተሸፈኑ ደኖችንና የደን መሬቶችን ጉዳዩ ከሚመለከተው አካል ተረክቦ ዘላቂነት ባለው መንገድ ያለማል፣ ያስተዳድራል፤

1. Establish and develop planting sites for the various tree species and those ones usable for the purpose of firewood, construction and manufacturing consumption as raw material sources;

2. Take charge of those forests capable of being used for production out of the forests under the ownership of the government and cause same to be utilized and exploited by preparing the appropriate management plan thereof;

3. Having identified those forestlands that would enable to develop forests and bring about economic benefits and thereby secured permission from the bodies concerned, carry out development activities thereof;

4. Cary out business activities in relation to the production and preparation of wild-gum, incense, bio-fuel and essential oil;

5. Supply the product to domestic and foreign markets by having planted factories and industries capable of processing and altering wood and non-wood forestry products into various kinds and categories of products;

6. Develop the tree species and other decorating tree and shrub seedlings and thereby conduct business activities therewith;

7. Take over those forests covered with incense and gum trees and forestlands from the organ concerned as well as develop and manage same in a sustainable manner;

8. ከፋብሪካዎችና ከኢንዱስትሪዎች ፍላጎት አንፃር የጥሬ ዕቃ ምንጮችን መሠረት ለማስፋት የሚያስችልና በአርሶ-አደሩ፣ በተቋማትና በአነስተኛ አልሚወች በኩል የሚካሄድን የደን ልማት ያበረታታል፤

8. Encourage the forestry development efforts to be carried out by farmers, institutions and small-scale developers with the view to enabling the expansion of raw material source-base from the standpoint of demands by factories and industries;

9. ከደን ልማትና ከእንጨት ሥራ ጋር ተያያዥነት ባላቸው ኬሚካሎችና ማቴሪያሎች ንግድ-ነክ ተግባራትን ያከናውናል፤

9. Undertake business-related activities as regards chemicals and materials having to do with the forestry development and wood works thereof;

10. አዋጭነቱን በማረጋገጥ የደንና የዱር እንስሳትን ልማት መሠረት ያደረገ የኢኮ-ቱሪዝም ሥራዎችን ያካሂዳል፤

10. Carry out the eco-tourism activities on the basis of forestry and wild animals development by ascertaining the feasibility of such tasks thereof;

11. በደንና በደን ውጤቶች ላይ በሚያተኩሩ የጥናትና ምርምር ተግባራት ይሳተፋል፣ ይደግፋል፤

11. Participate in and support the study and research activities that would focus on the forestry and forest products;

12. በደን ልማት ሥራዎች ላይ ለተሠማሩ ወገኖች የማማከርና የሥልጠና አገልግሎቶችን ይሰጣል፤

12. Render advisory and training services to those engaged in the forestry development activities;

13. ማሽነሪዎችን፣ ተሽከርካሪዎችንና ሌሎች ንብረቶችን እንዳስፈላጊነቱ ያከራያል፣ ራሱም ሊከራይ ይችላል፤

13. Lease out or itself obtain by rent machineries, vehicles and other properties, as deemed necessary;

14. ሰርቶ የሚያገኘውን ገቢ መሰረት በማድረግ ለስራ በሚያስፈልገው መጠን ካፒታሉ በየጊዜው እንዲጨምር ሊያደርግ ይችላል፤

14. Possibly cause its capital to be raised from time to time to the extent necessary for the duty, on the basis of the revenue it shall have generated out of its own effort;

15. የመካከለኛና የረዥም ጊዜ ብድሮችን በማጥናት ለባለስልጣኑ ያቀርባል፣ ሲፈቀድለትም ተግባራዊ ያደርጋል፤

16. በህግ-መሰረት የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፣

17. ዓላማዎቹን ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልጉትንና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸውን ተግባራት ያከናውናል፡፡

ክፍል ሶስት

ድርጅታዊ አቋምና አመራር

10. ድርጅታዊ አቋም

ኢንተርፕራይዙ በዚህ ደንብ መሠረት የሚከተሉት አበይት አካላት ይኖሩታል፡-

1. የስራ አመራር ቦርድ፣

2. በቦርዱ የሚሾሙ ዋና እና እንደ አስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ስራ አስኪያጆች፤ እና

3. ለስራው አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች የበታች የስራ ሀላፊዎችና ሠራተኞች፡፡

15. study and submit medium and long-term loans to the Regional Government and implement same up on approval;

16. Own property in accordance with law, enter into contracts as well as sue and be sued in its own name;

17. Perform such other activities as are necessary for the attainment of its objectives and other ones connected therewith.

PART THREE

ORGANIZATIONAL STATUS AND MANAGEMENT

10. Organizational Status

The Enterprise shall, pursuant to this regulation, have the following main organs:

1. The Board of Management;

2. A General Manager and, as deemed necessary, Deputy General Managers to be appointed by the Board; and,

3. Other subordinate heads and staff required for the duty.

11. ስለስራ አመራር ቦርዱ አሰያየምና የአባላት ጥንቅር

1. የኢንተርፕራይዙ ስራ አመራር ቦርድ /ከዚህ በኋላ "ቦርዱ" እየተባለ የሚጠራ/ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

2. የቦርዱ ተጠሪነት ለባለስልጣኑ ይሆናል፡፡

3. የቦርዱ አባላት ቁጥር ቢያንስ አምስት ሆኖ ከፍተኛው ደግሞ ከዘጠኝ ያልበለጠ ይሆናል፡፡

4. ሰብሳቢውን ጨምሮ የቦርዱ አባላት ከክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ጋር አስቀድሞ በሚደረግ ምክክር በባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር አማካኝነት ይሰየማሉ፡፡

5. ዋና ዳይሬክተሩ ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው የኢንተርፕራይዙን አንድ የሠራተኛ ማህበር ተወካይ የዚህ ቦርድ አባል አድርጎ ሊሠይም ይችላል፡፡

6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /4/ ስር የሠፈረው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የቦርዱ አባላት አሰያየምና አመራረጥ በሙያ፣ በስራ ልምድና በግል ብቃት ላይ ተመስርቶ የሚፈፀም ይሆናል፡፡

7. ለቦርዱ ሰብሳቢና ለአባላቱ ሊከፈል የሚገባውን አበል ባለስልጣኑ ይወስናል፡፡

11. Designation and Membership Composition of the Board of Management

1. A managing board of the Enterprise /hereinafter referred to as the **"Board"**/ is hereby established under this regulation.

2. The board shall be accountable to the Authority.

3. The number of members of the Board shall be at least five, but not exceeding nine.

4. Members of the board shall, including its chairperson, be designated by the Director General of the Authority in prior consultation to be conducted with the Head of the Regional Government.

5. The Director General may, where he finds it appropriate, designate a representative of the trade union of the Enterprise to be a member of the said Board.

6. Without prejudice to the provision laid down under Sub-Art. (4) of this Article hereof, the designation and selection of the Board members shall be conducted having due regard to their profession, work experience and personal competency.

7. The Authority shall determine the allowance appropriate to be paid for the chairperson and members of the Board.

8. የቦርድ አባላቱ የአገልግሎት ዘመን ከሶስት ዓመት የማያንስና ከአምስት ዓመት የማይበልጥ ይሆናል፤ ሆኖም አስፈላጊነቱ ሲታመንበት ማንኛውም የቦርድ አባል የአገልግሎት ጊዜው ሲያበቃ ለዳግመኛ ጊዜ ሊሠየም ወይም ሊመረጥ ይችላል፡፡

8. The term of office for the Board members may not be lower than three and not exceed five years; provided, however, that anyone of the Board members, whose official tenure has expired, may be re-designated or re-elected for the 2nd term, as deemed necessary.

9. ማንኛውም የቦርድ አባል አባልነቱን በገዛ ፈቃዱ ለመተው የፈለገ እንደሆነ ይኸው አባል በሌላ አባል እንዲተካ ጉዳዩን ለባለስልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡

9. Any member of the Board shall, where he wishes to voluntarily resign from such membership, submit the issue to the Authority so that the latter may be able to get him substituted with another member.

10. የኢንተርፕራይዙ የስራ እንቅስቃሴ ቀጣይነት ይኖረዉ ዘንድ የቦርድ አባላቱ የአገልግሎት ዘመን በአንድና በተመሳሳይ ጊዜ አያበቃም፡፡

10. The term of office of the Board members may not expire at one and the same time so that the functioning of the Enterprise would have continuity.

11. የቦርድ አባል የነበረ ማንኛውም ሰው በአባልነቱ ለመቀጠል የማያስችለው በቂ ምክንያት ሲኖር ዋና ዳይሬክተሩ ከክልሉ ርዕሰ-መስተዳድር ጋር በመመካከር በማናቸውም ጊዜ ከአባልነቱ ሊያነሳው ይችላል፤ ሆኖም ይህ ድንጋጌ በሰራተኛ ማህበር ተወካይነቱ የተሰየመን ማንኛዉንም የቦርድ አባል በሚመለከት ተፈፃሚ በሚደረግበት ጊዜ ማህበሩ ስለጉዳዩ አስቀድሞ እንዲያዉቅ መደረግ ይኖርበታል፡፡

11. Where there exists sufficient reason that renders any person who is a board member unable to carry on his membership, the Director General may, in consultation with the Head of Government, remove him from such membership; provided, however, that where this provision is applicable with regard to any board member who has been designated in representation of the trade union, the union shall be notified of the matter in advance.

12. የቦርዱ ስልጣንና ተግባር

ቦርዱ በዚህ ደንብ መሰረት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

12. Powers and Duties of the Board

The Board shall, pursuant to this regulation, have the following powers and duties:

1. በአዋጁ አንቀጽ 45 መሠረት ለባለስልጣኑ መቅረብ ከሚገባቸው በስተቀር በሌሎች የኢንተርፕራይዙ ፖሊሲ-ነክ ጉዳዮች ላይ ይመክራል፣ ውሣኔዎችን ያሳልፋል፤

2. የኢንተርፕራይዙን ዋናና ምክትል ዋና ስራ አስኪያጆች ይቀጥራል፣ ይመድባል፣ ደምወዝና አበላቸውን ይወስናል፣ ከስራ ያሰናብታል፤

3. የኢንተርፕራይዙን ሰራተኞች መዋቅር ያፀድቃል ደመወዛቸውን ይወስናል፡፡

4. ለኢንተርፕራይዙ ዋናና ምክትል ዋና ስራ አስኪያጆች ተጠሪ የሆኑ የስራ ኃላፊዎችን ቅጥር፣ ምደባና ስንብት መርምሮ ያፀድቃል፣ ደምወዝና ጥቅማጥቅሞቻቸውን ይወስናል፤

5. የኢንተርፕራይዙን የውስጥ ደንብ፣ የስራ ዕቅድና የማስፈፀሚያ በጀት ረቂቆች መርምሮ ያፀድቃል፤

6. የኢንተርፕራይዙን የረዥም ጊዜ ብድሮች ያፀድቃል፤

7. በኢንተርፕራይዙ ህልውና ላይ ወሳኝነት የሌላቸውን ቋሚ ንብረቶች ሽያጭ ያፀድቃል፤

8. የኢንተርፕራይዙ ሂሣቦችና ንብረቶች ባግባቡ መያዛቸውንና መጠበቃቸውን ያረጋግጣል፤

9. የኢንተርፕራይዙ ካፒታል ይጨምር ወይም ይቀንስ ዘንድ ለባለስልጣኑ ሐሣብ ያቀርባል፤

1. With the exception of those to be submitted to the Authority in accordance with Art. 45 of the Proclamation, deliberate and pass decisions on the policy-related issues of the Enterprise;

2. Recruit and appoint the General and Deputy General Managers of the Enterprise, determine their salaries and allowances as well as dismiss them from their respective positions;

3. Approve the structure of the employees of the Enterprise and determine their salaries;

4. Examine and approve the proposed recruitment, assignment and dismissal of those division heads accountable to the General Manager and Deputy General Managers as well as determine their salaries and benefits;

5. examine and approve the draft internal guidelines, work plan and implementation budget of the Enterprise;

6. Approve the long-term loans of the Enterprise;

7. Approve the sale of those fixed assets which may have no critical bearing on the existence of the Enterprise;

8. Ensure that the books of account and properties of the Enterprise are maintained and kept properly;

9. Submit a recommendation to the Authority as to whether the capital of the Enterprise should be increased or decreased;

10. የቦርዱን አመታዊ ዕቅድ አዘጋጅቶ ለባለስልጣኑ በማስፀደቅ ያስተገብራል፡፡

13. የቦርዱ የስብሰባ ጊዜና የውሳኔ አሰጣጥ ስነ-ስርዓት

1. ቦርዱ መደበኛ ስብሰባውን ቢያንስ በሶስት ወር አንድ ጊዜ ያካሂዳል፤ ሆኖም አስገዳጅ ጉዳዮች ሲያጋጥሙት አስቸኳይ ስብሰባዎችን ከዚህ ባነሰ ጊዜ ከማካሄድ አይታገድም፡፡

2. የቦርድ አባላት ስብሰባው ከመካሄዱ አስቀድሞ ረቂቅ የመወያያ አጀንዳው በፅሁፍ ተዘጋጅቶ እንዲደርሳቸው ይደረጋል፡፡

3. ከቦርዱ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በስብሰባው ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፡፡

4. ማናቸውም ጉዳይ ለቦርዱ ቀርቦ ከተመከረበት በኋላ በስብሰባው ላይ በተገኙት አባላት የአብላጫ ድምፅ የተደገፈ እንደሆነ የቦርዱ ውሣኔ ሆኖ ያልፋል፤ ሆኖም ድምጹ እኩል ለኩል የተከፈለ እንደሆነ የሰብሳቢውን ድጋፍ ያገኘው ሀሣብ የቦርዱ ውሣኔ ይሆናል፡፡

5. ቦርዱ ከኢንተርፕራይዙ ሠራተኞች መካከል ፀሐፊውን መርጦ ሊመድብ ይችላል፡፡

6. ፀሐፊው ቦርዱ የሚያካሂደውን የእያንዳንዱን ስብሰባ ቃለ-ጉባኤ በሚገባ ይይዛል፤ በስብሰባው ላይ የተገኙት አባላትም በቃለ-ጉባኤው ላይ ይፈርሙበታል፡፡

10. Prepare the annual plan of the Board and cause the implementation of same upon its approval by the Authority.

13. Meeting time and Decision-Making Procedure of the Board

1. The Board shall convene its regular meetings at least once in three months; provided, however that it may not be banned from holding extraordinary meetings in less than the prescribed time, whenever encountered with urgent issues.

2. The Board members shall be served with the draft discussion agenda prepared in writing ahead of the meeting having been held.

3. There shall be a quorum where more than half the members of the Board are present at the meeting.

4. Any issue shall, after having been submitted to and deliberated upon by the Board, be passed as the decision of the Board where it has been supported by the majority vote of members shown up at the meeting; in case of a tie, however, the motion having the support of the chairperson shall be the decision of the Board.

5. The Board may select and assign its secretary from among the employees of the Enterprise.

6. The secretary shall properly take down the minutes of each meeting to be held by the Board and thus, members showing up at the meeting shall put down their respective signatures thereon.

7. ቦርዱ የተሰበሰበበትን ቃለ-ጉባኤ 10 ቀን ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ለባለስልጣኑ ይልካል፡፡

8. የኢንተርፕራይዙ ዋና ስራ አስኪሃጅ በቦርዱ ስብሰባዎች ላይ ይሳተፋል፤ ሆኖም ቦርዱ በሚያሳልፋቸው ውሳኔዎች ላይ ድምፅ የመስጠት መብት አይኖረውም፡፡

9. በዚህ አንቀፅ ከዚህ በላይ የሠፈሩት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የራሱን ዝርዝር የስብሰባ ጊዜና የውሳኔ አሰጣጥ ስነ-ስርዓት መመሪያ ሊያወጣና በስራ ላይ ሊያውል ይችላል፡፡

14. ስለቦርዱ አባላት ተጠያቂነት

የቦርዱ አባላት የተሰጣቸውን ተግባርና ኃላፊነት በከፍተኛ ትጋት እና በብርቱ ጥንቃቄ መፈፀም አለባቸው፡፡ ይህንን ባለመፈፀማቸው በኢንተርፕራይዙ ላይ ለሚደርሰው ጉዳት በአንድነትና በነጠላ ተጠያቂዎች ይሆናሉ፡፡

15. ስለዋና ስራ አስኪያጁ ስልጣንና ተግባር

1. የኢንተርፕራይዙ ዋና ስራ አስኪሃጅ በዚህ ደንብ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

ሀ. የኢንተርፕራይዙን ስራዎች በሀላፊነት ያደራጃል፣ ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራልል፤

7. The Board shall refer the minutes of its sessions to the authority within the period of not more than 10 days from having held the meeting.

8. The General Manager of the Enterprise shall participate in the meetings of the Board; provided, however, that he may not have the right to cast a vote on the decisions to be passed by the Board.

9. Without prejudice to the provisions laid down under this Article hereof, the Board may issue its own specific meeting time and decision-making procedural guidelines and implement same.

14. Accountability of the Members of the Board

Members of the Board shall have to exercise the duties and responsibilities entrusted to them in great diligence and profound care. They shall be collectively and individually responsible for the damage sustained on the Enterprise as the result of their failure to discharge same.

15. Powers and Duties of the General Manager

1. The General Manager of the Enterprise shall, pursuant to this regulation, have the following specific powers and duties:

A. Responsibly organize, manage, coordinate and supervise over the activities of the Enterprise;

ለ. በዚህ ደንብ አንቀፅ 12 ንዑስ አንቀፅ (4) ስር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለእርሱና ለምክትሎቹ ተጠሪ የሆኑ የበታች የስራ ሀላፊዎችን ያስመድባል፣ ተግባራቸውን ይወስናል፤

B. Without prejudice to the provision laid down under Art. 12 Sub-Art. (4) of this regulation hereof, cause the assignment of subordinate division heads who are accountable to him and his deputies as well as determine their duties;

ሐ. በኢንተርፕራይዙ የውስጥ ደንብና አግባብ ባለው ህግ መሠረት ሌሎች የኢንተርፕራይዙን ሰራተኞች ይቀጥራል፣ ይመድባል፣ ያሰናብታል፣ ደምወዝና አበሎቻቸውን ይወስናል፤

C. Recruit, assign and dismiss other employees of the Enterprise pursuant to the internal guidelines of the Enterprise and pertinent law as well as determine their salaries and allowances;

መ. በኢንተርፕራይዙ ስም የባንክ ሂሣብ ይከፍታል፣ ያንቀሣቅሳል፤

D. Open and operate a bank account in the name of the Enterprise;

ሠ. ለኢንተርፕራይዙ ስራ ማስኬጃ የሚውሉ የአጭር ጊዜ ብድር ውሎችን ይዋዋላል፣ ቦርዱን በማስፈቀድ የረዥም ጊዜ ብድር ይወስዳል፣ ለእነዚሁ ዓላማዎች ቦርዱን እያስፈቀደ የኢንተርፕራይዙን የሚንቀሣቀስ ወይም የማይንቀሣቀስ ንብረት በዕዳ መያዣነት ሊሰጥ ይችላል፤

E. Conclude short-term contracts of loan to be used for operational expenditure of the Enterprise; enter into long-term loans upon the approval of the Authority and possibly use, for such purposes, movable and immovable assets of the Enterprise as collaterals for the payment of the debt by having obtained the approval of the Board;

ረ. የኢንተርፕራይዙን የስራ ፕሮግራምና በጀት እንዲሁም የውስጥ ደንብ ረቂቅ አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በስራ ላይ ያውላል፤

F. Prepare and submit the draft work program and budget as well as internal guidelines of the Enterprise to the board and put same into effect upon approval thereof;

ሰ. ቦርዱን በቅድሚያ በማስፈቀድ በኢንተርፕራይዙ ህልውና ላይ ወሳኝ ተፅዕኖ የሌላቸውን ቋሚ ንብረቶች ይሸጣል፤

G. having secured the prior approval of the Board, sell out those fixed assets which may have no critical bearing on the existence of the Enterprise;

ሸ. ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ኢንተርፕራይዙን ይወክላል፤

H. Represent the Enterprise in its dealings with third parties;

ቀ. የቦርዱን ውሣኔዎች ይፈፅማል፣ ያስፈፅማል፤

በ. የኢንተርፕራይዙን የስራ እንቅስቃሴዎች በሚመለከት በየወቅቱ ሪፖርት እያዘጋጀ ለቦርዱም ሆነ ለባለስልጣኑ ያቀርባል፤

ተ. ለስራው አስፈላጊ ሆኖ ባገኘው መጠን ከስልጣንና ተግባራቱ ከፊሉን ለኢንተርፕራይዙ የበታች የስራ ሀላፊዎችና ሰራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፤

ቸ. በኢንተርፕራይዙ የስራ እንቅስቃሴዎች ላይ የሚመክርና በርምጃውም ሆነ በዕቅዶቹና በውሣኔዎቹ ላይ የሚወያይ የስራ አመራር ኮሚቴ ሊያቋቁምና ስብሰባዎቹን በበላይነት ሊመራ ይችላል፤

ኀ. በቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተዛማጅ ተግባራት ያከናውናል፡፡

2. የኢንተርፕራይዙ ዋና ስራ አስኪያጅ ተጠሪነቱ ለቦርዱ ይሆናል፡፡

I. Implement and cause the implementation of the decisions of the Board;

J. Prepare periodic reports regarding the activities of the enterprise and submit same to the Board and the Authority;

K. Possibly delegate part of his powers and duties to the subordinate heads and employees of the Enterprise to the extent required for the duty;

L. Establish a management committee that may deliberate on the activities of the Enterprise and discuss on its proposed measures, plans as well as decisions and preside over the meetings of same;

M. Perform such other related duties as may be assigned to him by the Board.

2. The General Manager of the Enterprise shall be accountable to the Board.

16. ስለምክትል ዋና ስራ አስኪያጅ ስልጣን እና ተግባር

የኢንተርፕራይዙ ምክትል ዋና ስራ አስኪያጅ ተጠሪነቱ ለዋና ስራ አስኪያጁ ሆኖ የሚከተሉት ስልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. በኢንተርፕራይዙ ስራ አስኪያጅ ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

16. Powers and Duties of the Deputy General Manager

The Deputy General Manager of the Enterprise shall, being accountable to the General Manager, have the following powers and duties:

1. Carry out such duties as may be specifically assigned to him by the General Manager of the Enterprise.

2. የኢንተርፕራይዙ ዋና ስራ አስኪያጅ በማይኖርበት ወይም ስራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜና ሁኔታ እርሱን ተክቶ ይሰራል፤ ሆኖም በድርጅቱ ውስጥ ከ1 በላይ የሆኑ ምክትል ስራ አስኪያጆች ያሉ እንደሆነ ከመካከላቸው በሹመት ቀደምትነት ያለው ምክትል ዋና ስራ አስኪያጅ ዋና ስራ አስኪያጁን ተክቶ ይሰራል፡፡

2. Act on behalf of the General Manager of the Enterprise in his absence or under the circumstances where and when he is unable to perform his normal duties; provided, however, that where there are more than one deputy managers in the Enterprise, the deputy manager who has seniority in an appointment shall act on behalf of the General Manager.

17. ስለ ዋና ስራ አስኪያጁ እና ምክትል ዋና ስራ አስኪያጆች ኃላፊነትና ተጠያቂነት

የኢንተርፕራይዙ ዋና ስራ አስኪያጅም ሆነ ምክትል ዋና ስራ አስኪያጆች ተግባራቸውን በሚፈጽሙበት ጊዜ ሆነ ብለው ወይም በቸልተኝነት በኢንተርፕራይዙ ላይ ለሚያደርሱት ጉዳት ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡

17. Responsibility and Accountability of the General and Deputy General Managers

The General Manager and the Deputy General Managers of the Enterprise shall be liable for any harm they intentionally or negligently commit against the Enterprise while performing their respective duties.

ክፍል አራት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

PART FOUR

MISCELLANEOUS PROVISIONS

18. የሂሳብ መዛግብት

1. ኢንተርፕራይዙ የተሟሉ፣ ትክክለኛ የሆኑና በንግድ አሠራር ተቀባይነት ያላቸው የሂሳብ መዛግብትን ይይዛል፤

2. የኢንተርፕራይዙን የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ-ሠነዶች አያያዝ በተመለከተ ባለስልጣኑ የሚያወጣቸውን መነሻ መመሪያዎች መሰረት በማድረግ ቦርዱ ዝርዝር መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፤

18. Books of Account

1. The Enterprise shall maintain and keep complete and accurate books of account that are acceptable to the commercial working practice;

2. The board may, pursuant to the initial directives to be handed down by the Authority, issue specific guidelines regarding the keeping of the books of account and finance-related documents;

3. ኢንተርፕራይዙ ቢያንስ በሂሳብ አመቱ አንድ ጊዜ ሂሳቡን መዝጋት አለበት። ሂሳቡን የመዝጋቱ ተግባር የሂሳብ አመቱ በተጠናቀቀ በሶስት ወር ጊዜ ዉስጥ መሆን ይኖርበታል።

19. ስለሂሳብ ምርመራ

የኢንተርፕራይዙ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብም ሆነ ንብረት ነክ ሰነዶች ባለስልጣኑ በሚሰይማቸው የውጭ ኦዲተሮች በኢንተርፕራይዙ የሂሳብ ዓመት መጨረሻ ላይ ይመረመራሉ፤ ጉዳዩ ውስብስብ በሆነ ጊዜ ባለስልጣኑ የክልሉን ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ድጋፍ ሊጠይቅ ይችላል።

20. ስለትርፍ ድርሻ ክፍያ

ኢንተርፕራይዙ የሂሳብ ዓመቱ ከተጠናቀቀበት ጊዜ አንስቶ ባሉት የሰባት ወራት ጊዜ ውስጥ የክልሉን መንግስት የተጣራ ትርፍ ድርሻ ባለስልጣኑ በሚወስነው መጠን መሰረት በዓመቱ ውስጥ ያገኘውን ትርፍ በክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ በኩል እያስፈቀደ መልሶ የደን ልማት ስራዎችን ያካሂዳበታል።

21. ስለተሻሩና ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች

1. የክልሉን ደን ኢንተርፕራይዝ ለማቋቋም የወጣው ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 70/2002 ዓ.ም. ተሽሮ በዚህ ደንብ ተተክቷል።

3. The Enterprise shall have to close the account at least once in the fiscal year. The task of closing the account ought to be within the period of three months from the date of the fiscal year having been completed.

19. Auditing

The books of account and financial as well as property related documents of the Enterprise shall be audited by those External Auditors to be designated by the Authority at the end of the Enterprise's fiscal year. The Authority may request the Office of the Auditor General of the Regional State for support, when the case is found to be complicated.

20. Payment of Dividend

The Enterprise shall, pursuant to the rate to be set by the Authority, cause the undertaking of forestry development with the profit that it has obtained within the year, by having got the permission of the Regional Finance and Economic Cooperation Bureau, the net dividend share of the Regional State within the period of seven months starting from the date on which the fiscal year has come to an end.

21. Repealed and Inapplicable Laws

1. The Council of Regional Government Regulation issued to provide for the Establishment of the Regional Forestry Enterprise Regulation No. 70/2009 is hereby repealed and replaced by this Regulation.

2. ይህንን ደንብ የሚቃረን ማናቸውም ሌላ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የተለመደ አሰራር በዚህ ደንብ ውስጥ በተሸፈኑት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

22. መብትና ግዴታን ስለማስተላለፍ

ቀደም ሲል በደንብ ቁጥር 70/2002 ዓ.ም መሰረት ተቋቁሞ ሲሰራ የቆየው የክልሉ ደን ኢንተርፕራይዝ መብቶችና ግዴታዎች በዚህ ደንብ እንደገና ወደ ተቋቋመው አዲሱ ኢንተርፕራይዝ ተላልፈዋል።

23. መመሪያ የማውጣት ስልጣን

ቦርዱ ይህንን ደንብ በተሟላ ሁኔታ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉትን ዝርዝር መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል።

24. ደንቡ ስለሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በክልሉ መንግስት ዝክረ ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ባህር ዳር
መጋቢት 22 ቀን 2010 ዓ.ም
ገዱ አንዳርጋቸው
የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ርእሰ-መስተዳድር

2. No other regulation, directive or customary practice inconsistent with this regulation shall be applicable with respect to the matters covered therein.

22. Transfer of Rights and Obligations

The rights and obligations of the existing Forestry Enterprise which has previously been established pursuant to the Regulation No. 70/2009 are hereby transferred to the new Enterprise re-established under this Regulation.

23. Power to Issue Directives

The Board may issue specific directives necessary for the full implementation of this Regulation.

24. Effective Date

This regulation shall come into force as of the date of its publication in the Zikre-Hig Gazette of the Regional State.

Done at Bahir Dar
This 31st day of March, 2018
Gedu Andargachew
Head of Government of the Amhara National Regional State